Sunday, August 2, 2009
ዳኮታ የጥናት መአከል

## ለሱማሌ መፍትሄ የአራትዮሽ ውይይት መጀመር ያስፈልጋል

(አልሽባብ፤ ኢትዮጵያዊ ሀይል፤ የኤርትራና የአሜሪካን መንግስት።)

ሱማሌ የአልሽባብ ተዋጊዎች 98% እነመለስና አሜሪካኖች ሊያቆሙት የሚፈልጉት መንግስት ሁለት ፐርሰንቱን የሱማሌ ግዛት ተቆጣጥሮ ነው ያለው። መንግስት ተብዬው እራሱን ከአልሽባብ ታጋዮች ከመከላከል በስተቀር ለማጥቃትና ይዞታውን ለማስፋፋት ምንም አቅም የለውም። እሰከጭራሹም ሱማሌን ለቆ እንዲወጣ ቀነ ቀጠሮ እየተቆረጠለት ነው ያለው። የበዙት የህዝብ ተወካዮች፤ የመንግስቱ በአለስልጣናት ወደተለያየ አገር ጥለው ፈርጥጠዋል።

በኦባማ አስተዳደር ተጽኖ መለስ የኛን ጦር በድጋሚ ሱማሌ እንዳስገባ ከተሰማ ቆየት ብሏል። እነመለስ ላጭር ጊዜ የማጥቃት ዘመቻ ይባሉ እንጂ በመሬት ላይ ካሉት ምክንያቶች ተነስቶ ለረጅም ጊዜ ሱማሌ ውስጥ እንደምንዳክር መገመት ይቻላል። የአሚሪካኖቹ ተእዛዝ ቀጭን ባይሆን አሁን መለስ የሱማሌ ጉዳይ ውስጥ ተመልሶ በአይዶል ለስልጣኑ እንደሚሻል ያሰላ ይመስላል። አለቆቹ ሙሉ ለሙሉ ፊታቸውን የሚያዞሩበት ከሆነ ግን ትንሽ የስልጣን እድሜውን ለማራዘም ለሁለተኛ አይደለም ለአምስተኛ ጊዜ ግባ ሲባል ጦሩን ሱማሌ ከመላክ ውጪ ምርጫ አልነበረውም።

የመለስን የሱማሌ ወረራ ሲጀመር ጀምሮ ትልቅ የተሳሳተ እርምጃ ከመሆኑ አኳያ እሬሳቸው ከሚጎተተው ዜጎቻችን ደህንነትም፤ ለሱማሌ ወንድሞቻችን ካለ ተቆርቋሪነት ወረራውን ለማስቆም አይደለም ተቃወምነው በሚያሰኝን ሀይል ያደረግነው ነገር የለም። እንደተቃዋሚም ስልጣን ላይ ያለው አንባገነን የሰራው አንዱ ትልቅ ስህተት እንደመሆኑ ጉዳዩን በአግባቡ ትግሉን በሚያግዝ መንገድ ተጠቅመንበታል ማለት ያስቸግራል። አሁንም በአግባቡ ይህ ጉዳይ ጊዜ ተሰቶ እየታሰበበት ያለ አይመስለንም። ለኛ የሱማሌ ጉዳይ በሁለት በኩል ስለት ያለው ቢለዋ ነው። እንድንቆረጥበት ወይ እንድንቆርጥበት የሚያደርገን እጃችንን በአግባቡ እጀታው ላይ ማሳረፋ በመቻላችንና እጀታውን በአያያዛችን ነው የሚወስነው። ለአሁኑ የቢለዋው እጀታ ላይ የአቶ መለስ እጅ ብቻ ነው ያለው።

የኤርትራ መንግስት በግልጽ የአልሽባብ ተዋጊዎችን ይደግፋል። ኢሳያስ ለሱማሌዎች እየዋለ ካለው ውለታ አኳያ የአልሽባብ አመራሮች ሊያዳምጡ ከሚችሏቸው ሰውች ኢሳያስ ዋንኛው ነው። ማዳመጥ ብቻ ሳይሆን የሆነ የሚያሰራ አንድ አይነት ስምምነት ለመቋጨት ለሚፈልግ ቡድን ወሳኝ መንግስት ነው።

መለስን በሚገባው ላሉ ጽሁፉ አይመለከትም። ሱማሌዎቹን ታንካችሁን ለሳምንት አውሱንና ጠቅ ጠቅ አርገን እንመለስ ደረጃ ባይሰሩ ስራ እየተሰራ አይደለም ብለን ያስገርመናል። የዚህ ጽሁፍ አላማ ከዚህኛው አላማ ውጪ ሊሰራ የሚገባ ስራና፡ ስራውን ሊሰራ የሚችል ስብስብ አስፈላጊነት ስለታየን ነው።

የሱማሌ ችግር መፍትሄ ማግኘት ላይ ቀጥተኛ ፍላጎት ያለው አራት አካል አለ። 1.ሱማሌዎች(አልሺባብ)፤ 2.ኢትዮጵያዊያን( እነመለስን አይጨምርም)፤ 3.አሜሪካን መንግስትና፤ 4.የኤርትራ መንግስት። የሱማሌ ችግር መፈትሄ በማግኘቱ ተጠቃሚ የማይሆነው የመለስ መንግስትና በቁሙ እየሞተ ያለው የሱማሌ መንግስት ተብዬ ብቻ ነው። የሱማሌ ችግር ላይ መፍትሄ በመስራቱ ደግሞ በምንም አይነት ሂሳብ ከሱማሌዎቹ ቀጥሎ ተጠቃሚዎች እኛ ነን። አለ የምንለውን የኤርትራን መንግስት ጥቅም መጨረሻው ድረስ ወስደን በናየው የሚደግፈው ሀይል ባያሸንፍ ምን ያገኛቸዋል?። ኤርትራ ጉዳዩ ላይ ስላለችበት ብለን እኛ ጉዳዩ ላይ ያለንን ቀጥተኛ ፍላጎትና ጥቅም እንደሌለ ወይ አሳንሰን ብናየው አሁንም ለወደፊቱም አሉታዊ ውጤት ያለው ስህተታችን ነው የሚሆነው። የሱማሌ ሰላም ማግኘት ችግሮች ላይ መፍትሄ መሻት መስራት ለሱማሌዎቹ ወይ ለአሜሪካኖቹ ይሰሩታል ብለን የምንተወው ጉዳይ በፍጹም አልሆነም።

*እኛን ማን ይወክል የሚለው የሚያሳስብ ነው። ይህን ስራ ሊሰራ የሚችል አግባብ ያለው አካል የለነም። ደጋግመን እንዳስገነዘብነው ሁሉን ያካተተ ትብብር ጠቃሚነቱ ለእንደዚህ አይነት ጉዳዮች ነው። እኛ ያለንበት ችግር ይዘቱ የተለየ ነው። ኢትዮጵያዊ የሆነ ለአገሩ ሉአላዊነት የሚያስብ ለህዝቦቿ ደህንነት ለሚመጣውም ትውልድ የሚጨነቅ የተሰባሰበ፣ ሁሉ ሊሰማው የሚችል፣ እንደመንግስት መተወን የሚችል ተቃዋሚ መፍጠር፣ ማውጣት እንችል ይሆን እንጂ ለእንደዚህ አይነት መንግስት እንደው አልታደልንም። እነሱ ሲፈጠሩ ጀምሮ ካራመዱት። ከአስራ ሰባት አመት የአዲስ አበባ ቆይታቸው እየሆነ እየተነገሩ ካሉት ነገሮች ያልቆረጠለት ኢትዮጵያዊ የልጅነት እድሜ ላይ ያለ ካልሆነ በርግጠኝነት እብድ መሆን አለበት። በዘር ጭንቅላት በማሰብ ከሚታወቁት ውስጥ ወይ እያወቀ በፍረሀት ወይ ለጥቅም ሲል የሚያስመስለውን ሆዳም ሳይጨምር ማለት ነው።*

*አገራችን ላይ ያለው መንግስት ኢትዮጵያዊ ስሜት የሌለው መሆኑ ምኑ ይግረማል። የዚህ አይነት መንግስት አለመኖሩና ችግሩን ተረድተው የአገሪቷን ብሂራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ ያን ክፍተት ሊሞሉ የሚፈልጉ የሚመስሉ ተቃዋሚዎች መኖራቸው ግን ተሰባስበው ሊያደርጉት ካልቻሉ ልዩነታቸው ምኑ ላይ ነው የሚለውን ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርመ። ሁሉንም በጋራ መውቀጥ እንዳይሆን እንጂ ለኛም ልዩነቱ ግራ እየገባን ነው። ተቃዋሚዎቻችን እርግጠኛ ነን ትችታችን አልሰላም። ለነገሩ በገኘነው አጋጣሚ ይጠቅማል ብለን ያሰብነውን ይህን ሀሳብ እንደምንገፋበት በግልጽ ቀድመንም ተናግረናልና ትረዱናላችሁ። ይህን ሀይለ እንዲፍጠር ግፊታችን ላይ ሚዛናዊ እንዲያስመስለን ነው እንጂ እያንዳንዱን ተቃዋሚ በተናጠል ልናውቀው እየሞከርን ነው። መተባበር ለምን አልቻልንም ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት ግድ ነውና።*

*ከጊዜ ጋር ውድድር ውስጥ ካልገባን። የመለስ ቡድን በአገርና በህዝብ ስም ብዙ ጎጂ ስምምነቶች እያደረገ ነው። እኛ ተሳክቶልን ስንሰራው አንድ ቀን መቼም አይቀርም!! ጥፋቱ መጥፋት የሚችለው ድረስ የጠፋ ነው የሚሆነው። በኋላ መለስ በገባቸው ስምምነቶች ብድሮች አንስማም ለማለትም ሁሉ የተወከለበት የተቃውሞ ድምጽ በአስቸኳይ ካስፈለገን አመታት አለፉል።*

## <u>መፍትሄ መፈለጉ ያሉ አጋዥ አበረታች ሁኔታዎች ።</u>

ሀ. እድሜ ለነጀንዳይ ፍሬዘር እንጂ እስላሚክ ሸንጎው ከአሜሪካኖቹ ጋር ለመነጋገር ፍቃደኛ ነበር። ሱማሌዎች እንደማንም ህዝብ ሰላምን አግኝተው መንግስት አቁመው ህዝባቸው ከመከራና ከስደት ለመገላገል ፍላጎት የላቸውም ብሎ ማሰብ አይቻልም። አልሸባብም አፍንጫ ላይ ደርሶ ከዛሬ ነገ ያለምኩትን አሳለካው እያለ እድሜውን ሲቆጥር የወደፊቱ የሚያመጣውን እርግጠኛ መሆን አይቻልምና አቋራጭ መፍትሄ ከተገኘ አይጠላም። ከማንም በላይ የሆነ አይነት ስምምነት ይሻል። ላሜሪካኖቹም በሚመች መንገድ ሊላዘብ ይችላል።

ለ. አሜሪካኖቹም ከመሰረታዊ እምነታቸው ውጪ ሱማሌ ውስጥ ሊያቆሙት ስለሚፈልጉት መንግስት ሲሉ ከአንባገነን ከወንጀለኛ ጋር ከሚሞዳመዱ ሁሉ አሸናፊ ነኝ ለሚልበት ስምምነት ፍቃደኛ ሊሆኑ ይችላሉ። በድን የሆነን መንግስት ይዘው ከሚንገታገቱ በከፊልም ቢሆን ሊታመኑበት የሚችልን የበዛውን ሱማሌ የያዘ አካል ጋር ስምምነት መቁረጥ የኦባማ አስተዳደር ሊያራምድ ከሚፈልገው ለውጥ አኳያ ትክክለኛ አቋም ይመስላል።

ሐ. የኤርትራ መንግስት ዲፕሎሚሳዊ ችሎታ  አኳያ እስከዛሬም ውጤታማ እንዴት እንዳልሆኑ ይገርማል። ሱማሌዎች ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍ ለመታደግ ሱማሌዎችን እራሳቸውን እንዲከላከሉ ከማገዝ ጎን ለጎን ከአሜሪካኖቹ ፍላጎት ጋር ለማቀራረብ የጣሩ አይመስለም። ለኤርትራ ከውጤቱ ተጠቃሚ ከመገለል መውጫም እንደሚሆን ለመረዳት አያስቸግርም፡፡ ሊያስማማ በሚችል መንገድ ትርጉም እንዲስጥ አድርጎ መፍትሄ ለመስራት ለመሞከር ፍቃደኝነቱ ካለው ጋር የመሪነቱን ቦታ ይዞ የጎላ አስተዋጾ ለማድረግ እንቢ የሚሉ አይመስልም። እውነትን ለብቻ ስለያዙ ብቻ የተፈለገውን ውጤት ማስገኘት በቀጥታው መንገድ አሁን በአለንበት አለም ሁሉ እንደማይደረስ ቢያደርስም ከፍ ያለ ዋጋ እንደሚያስከፍል የማወቅ ችግር የኢሳያስ አስተዳደር ላይ አይታየንም።

መ. ከጥቅማችን አኳያ ለኛ ጉዳያችን ነው። የሱማሌ ጉዳይ ላይ ተመራማሪ መፍትሄ አመንጪ የመሀል ሰው፤ ግፊት አድራጊ ብዙ ብዙ መሆን አለብን። ደስ የሚለው ሊሰራው ውጤት ሊያመጣ የሚችል በአለ እውቀቶች አሉን። የሱማሌ ጉዳይ ማሰብ ነው የጎደለው። እዛ ላይ ከፍ ያለ አስተዋጾ አድርገን የጎደለውን ልንሞላው እንችል ይሆናል። እኛ ሰርተን ልናመጣ እንዲሆን ከምንፈልገው  የኛ ጥቅም ድብቅነት የሌለው አግባብም የሆነ ነው። ግልጽ ሆነን እስከቀረብን በሁሉም አካላት ተቀባይነት በቀላሉ ማግኘት እንችላለን የሚል ግምት አለን። ፍላጎታችን ግልጽ ስለሆነ በምንም አይን ልናደርግ የምንፈልገውው አስተዋጾ በመጥፎ አይታይም።

ውጤታማነታችን ከምናዘጋጀው ዝርዝር የስራ አፈጻጸም፤ አቀራረባችን በምንጠቀምበት ቃለት ግልጽነትና ጥናታቂ የወሰናል። ማን ይስራው የሚለው መልስ ማግኘት ያለበት ነው። የስራ መደራረብ እንዳይኖርባቸው ሊሰሩት የሚችሉትን በምስራቅ አፍሪካ አካባቢ እውቀት ያላቸውን በአለ እውቀቶቻችንን በመሰብሰብ እንኳ እየተሰባሰቡ ያሉት የስቪክ መህበራትና ምሁራኖች ሀላፊነቱን ቢወስድ ብለን ጥቆማችንን እንቀርባለን። እንዴት የሚለው ዝርዝር ውስጥ ያልገባነው የተሻለ ሊሰራው የሚችል ጭንቅላት አለ ብለን ስላሰብን ነው። ኢትዮጵያ ይህን የመከራ ጊዜ የምታልፈውም የአገራችንን ሁኔታ ያሰበ ሁሉ ተስፋውን የሚያደርገው ተቸግሩ በደህና ጊዜ በአፈራቻቸው በአለእውቀቶቿ ነው፡፡

ከዚህ በፊት በተወሰነ ደረጃ  የኢትዮጵያ ሪሺው ኤልያስ ክፍሌ ጨምሮ የነበረበት የሱማሌ ጉዳይ ላይ ተጅምር ነበር ከሱማሌዎች ጋር የመቀራረብ ሙከራ ነበር። የት ደረጃ እንዳለ አሁን በአናውቅም ስራውን ሀላፊነት ወስዶ ሊሰራው ፍቃደኛ ለሆነው አካል መነሻ ቦታ ሊሆን ይችል ይሆናል የሚል ግምት አለን።

<u>ይህን ለማሰብ ምክንያት የሆኑን ነገሮች።</u>

ወያኔ ስልጣን ላይ እስካለ ሱማሌ ውስጥ አለመረጋጋት ይኖራል። ሱማሌ ጦርነት እስካለ

መለስ ከአሜሪካን ድጋፍ ያገኛል። አለመረጋጋት ሱማሌ ውስጥ እንዲኖር የመለስ መንግስት የሚፈልገው ነው። መቸም ትክክለኛ መፍትሄው ላይ እንዲሰራ ፋላጎት አይኖረውም። መለስን ስላጣን ላይ ለመቆየት ሲባል የሱማሌ ህጻናት አሮጊቶች ሳይቀሩ በመድፍ ይደበደባሉ በቦንብ ይጋያሉ። አገራቸውን ትተው ይሰደዳሉ። አገራቸው የእምድር ላይ ያለ ገሀነም ሆኗል። ከሱማሌ ጓደኞቻችን እንደምንሰማው ስረአት አልበኝነቱ ከመብዛቱ የተነሳ ወንዶች ብቻ አይደሉም የተከናነቡ ሴቶች በቡድን ሆነው በመሳርያ አስገድደው የሚዘርፉበት የሚደፍሩበት አገር ሆኗል። በሌላ በኩል ኢትዮጲያዊው የደሀ ልጅ መለስን ስልጣን ላይ ለማቆየት ስለጠቀመ በሱማሊያ እሬሳው ይጎተታል፤ ይቆስላል። ያልሞተውም በጦርነት ወላፈን ይለበለባል። መቆመር በሚችልው የመጨረሻ ደረጃ ድረስ በዜጎቻችን ሂወት መለስ እየቆመረ ነው።

ምርጫ 97 ወያኔዎች የገጠማቸውን ሽንፈት ያን ተከትሎ ስልጣን ላለመልቀቅ ሽንፈታቸውን ላለመቀበል እነመለስ ያደረጉት ጭፍጨፋ። ሱማሌ ውስጥ አሜሪካኖች አለን የሚሉት ስጋት (የእስላሚክ ሸንጎው መላውን ሱማሌ መቆጣጠር) ጋር ተገጣጠመ። ይህን አጋጣሚ አሜሪካኖች እነመለስንም እኛንም እነሱን ተጠቃሚ በሚያደርግ መንገድ ተጠቀሙበት። መለስ ተደራድሮበት ስለነበር ስልጣኑን በማቆየት ከሂደቱ አትራፊ ሆነ። እኛ ለነጻነታችን ከአሜሪካም ጋር መታገል ግድ ሆነብን።

ኦባማ ወደስልጣን ነገሮችን በአልተሞከረ ለየት ባለ መንገድ እንደሚሰራ ብዙ ተናግሮ ነው ስልጣን የያዘው። መለስ በዛኑ ሰሞን ከሱማሌ መውጣቱን አወጀ። የመለስን ከሱማሌ መውጣት ተከትሎ በራቸው ድረስ ተሄዶ ሲጮህ አልሰማ ያሉ የውጪ ሚዲያዎች ስለኢትዮጲያ ለመዘገብ ቻሉ። ከሱማሌ ሳይፈቀደልት ጦሩን ከማውጣቱ በተጨማሪ ሊያጠቁት የሚፈልጉትን የሱዳን መሪ አልበሽርን ለመያዝ ይታዘዘናል ብለው ሲጠብቁት ባሳየው ጥጋብ ሽረሪት አድርቶበት የነበረው የጋንቤላ ጭፍጨፋ የክስ ዶሴ ሁሉ ወጣ።

መለስ ከሱማሌ ሲወጣ ችግሩ ሲገባ የነበረበት ቦታ ዞሮ እንደሚመለስ ያውቃል። ይህን ህጻኑ አቡሽም የሚያውቀው ነው። የሱማሌ ሁኔታ ለአሜሪካኖች ምቾት እንደማይሰጣቸው ግልጽ ነው። የሱማሌ ጦርነት እኛ ተዋጋነው እንጂ የነሱ ነው። ለአሜሪካን ሁለተኛውን ሽንፈት ተሸነፍንላቸው ማለት ነው። ጦርነቱን እንጂ ሽንፈቱን በስሜት ይጋሩናል። ሆኖም ግን አሁንም እነሱ የማይሞቱበት እስከሆነ ሊዋጋላቸው ፍቃደኛ እስካለ ለሶስተኛ አይደለም ለአስረኛም ጊዜ አሸናፊነት እስኪሰማቸው ይሞክራሉ። ወንድሞቻችንን ሱማሌ ወስዶ ለሁለት አመት ለማዋጋት ለመሪያችን ለፕሬዘዳንት መለስ ዜናዊ የሚከፈለው ገንዘብ እንደው ከገቢው ወጪው ሳይቀነስ እንኳ ብዙም አታስገባም ከምትባለው ከሳውዝ ዳኮታ ክፍለ ሀገር በአንድ ቀን የአሜሪካን መንግስት የሚያገባው ገቢን አያህልም። ከገንዘብ አኳያ እነሱ ለመለስ መንግስት የሚያወጡት እሚንት ከመሆኑ የተነሳ ስራ ለንጀራ ነው።

በተለየ ግን ለኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚንስተር ለአቶ መለስ ዜናዊ የሚሰጣቸው ትልቁ ስጦታ ያልተመረጥክ፣ አንባገነን፣ ነብሰ ገዳይ መሆንህን እናውቃለን ግን ዝም እንላለን እዚህ አርስት ላይ አናወራምን ነው። እውነቱን ለመናገር ግን ለአሜሪካኖቹ ለመለስ መንግስት እየከፈሉት ካለው ገንዘቡ በኢትዮጵያ ህዝብ ነጻነት ምርጫ ላይ መደራደራቸው፣ ከነብሰገዳይ ጋር ማበራቸው እየሰቀጠጣቸው ምቾት አልሰጥ እንዳላቸው ከኋላ ሆነው ከመድበስበሳቸው ማወቅ ይቻላል። ከተጠያቂነትም ለመሸሽ እንዲያመቻቸው አርገው ነው

መለስን እየተጠቀሙበት ያሉት። የሽብርተኛ ጦርነት ባሉት ዘመቻ የኢትዮጵያን ያህል ኢንግላንድም አጋር አልሆነችም። ማንም መሪ መለስ ያጎበደደውን ያህልም ለመተባበር ወገቡ አልተሰበረም። ያም ሆነ እንኳ ይህ ግምት ውስጥ ገብቶ አፍሪካዊቷ ዲሞክራቲክ አገር ጋና እንጂ መለስ እመራዋለው የሚለው አገር አይደለም ኦባማ ሊጎበኝ የሄደው። ወይ ሂለሪ የምትሄደው። እነዚህን ከመሳሰሉ ብዙ ምክንያቶች ተነስተን በአንጻራዊ ስናየው መዋጫ እንጂ መገላመጫ አንገት ካልፈጠረባቸው የኛዎቹ ከትግራይ በወጡ መሪዎቻችን እናፍራለን። ያማይመለከትን ጦርነት ውስጥ አገሪቷን ዶለው የደሀ ልጆችን እሬሳ ሲያስጎትቱ የጥፋተኝነት ስሜት የማይሰማቸው ደነዞች ናቸውና።

ኦባማ የሚያወራውና በተግባር የሚሰራው ኢትዮጵያን በሚመለከት በይገናኝ የሚቸግረው ነገር ሊኖር እንደሚችልም ማሰብ ይሻል። ለተሳሳተ የመንግስቱ ውሳኔ ተጽኖዎች እንዳሉ ማወቅ አለብን። በግል በርግጠኝነት ስለኢትዮጵያ ሁኔታ ያውቃል። በአካልም ተነግሮታል ችግራችንን ይጋራል። እኛ ስንበረታና ለመሰማት ስንሞክር ነው ሊያግዝ የሚችለው። የተሻሉ አማራጮችን ማሳየት አለብን። የሱማሌ ጉዳይ ላይ መፍትሄ ለመሥራት የኦባማ መንግስት አይፈልግም ብሎ በደፈናው ማሰብ ግን ስህተት ነው የሚሆነው። ከችግሩ ፈጥኖ ማደግና እሱ ወደስላጣን የመጣበት ጊዜ ከጠቅላላ የአሜሪካ ፖለቲካ ሁኔታ አኳያ በአሜሪካኖቹ አይን ሱማሌ ውስጥ አለ ከሚሉት አደጋ ጋር ነው አብረን ማየት ያለብን። የሱማሌን ችግር አሜሪካኖቹን ምቾት በሚሰጣቸው መንገድ ለመፈጸም ሊሎች የተሻሉ መፍትሄዎች በፊትም ነበሩ። አሁንም ይኖራሉ። እነዛን የተሻሉ መፍትሄዎችን ለማየት ግን ድፍረት ቢመስልብንም እስቴት ዲፓርትመነት አካባቢ በይበልጥም የምስራቅ አፍሪካ አካባቢ የሚሰሩት ላይ የእውቀት ችግር ያለ ነው የሚመስለው። የኤርትራ መንግስትም የዲፕሎማሲያዊው ስራ ላይ ድክመት ይታያል።

ለማንኛውም እኛ ትግል ላይ ነው ያለነው። የሚታገል ሰው ደግሞ ትግል ላይ ከሚፈጠሩ መልካም አጋጣሚዎች አይደለም ከመሰናክሎቹ ከችግሮቹም ትግሉ የሚጠቀምበትን ነገር መፈለግ አለበት። አጢነን ከአየነው የወያኔ መንግስት ሱማሌ በመግባቱ ከአሜሪካን እርዳታን አግኝቶ የነጻነት ትግላችን ላይ ከሚያሰድረው ተጽኖ መለስ ከወሰደው በዚህ የተሳሳተ እርምጃ ትግሉ ሊጠቀምበት የሚችለው በአለ ብዙ አጋጣሚ ነበር አሁንም አለ። ተቃዋሚዎቻችን በድርጅት ደረጃ አንድ ላይ ሆነው አጋጣሚውን ሊጠቀሙበት አልቻሉም። ሁሉ ሊስማማበት ይገባ የነበረው የሱማሌ የመለስ ወረራ እንኳ ከአገርቤት የልደቱ ፓርቲና ከውጪ የዶ/ር ነገደን ህብረት (ኢህአፓን አይጨምርርም በጊዜው የህብረቱ አካል የነበረ ቢሆንም ) የሱማሌ ወራራ እሰየው የኦጋዴን ነጻ አውጪን ስለሚያጠፋ የመሰለ ምክንያት የተሰጠበት ነው። ስለተሳሳተ ውሳኔያቸውም ልደቱን ብንተወውም ህብረቶች በከፊልም ቢሆን ሀላፊነት መውሰድ አለባቸው። ምክንያቱም የደሀ ልጆች እሬሳ በሰው አገር ተጎትቷል። የኦጋዴን ወንድሞቻችን ሴት ህጻን ሽማግሌ ሳይል መለስ አስፈጅቷል። ሱማሌ ስደተኛ የነበሩ ዜጎቻችን ታድነው ተገለዋል፤ ደብዛቸው ጠፍቷል። የተገኘው ድምር ውጤት ከበፊቱ የባሰ አክራሪ የሱማሌን 98% መሬት ተቆጣጥሮ ነው ያለው። የኦጋዴን ነጻ አውጪም ትግሉን አጠንክሮ ቀጥሏል። ከሱማሌ ወንድሞቻችን ብዙ መዘዝን የሚያመጣ ቁርሾ ለሚመጣው ትውልድም የድርሻው አስቀምጠናል።

ሱማሌ ላይ ህብረቶች ከያዙት አቋም በተጨማሪ ህብረቱ ትግሉ ላይ ካለው አንጋፋ እድሜ አኳያ እድገት ላለማሳየቱ ምክንያቶቹ ግልጽ እየሆኑ ነው። በሌሎች የገራችን የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ካራመዷቸው አቋሞች ከመግለጫዎቻቸው መረዳት እንደሚቻለው ትግሉን

ከማገዝ ረገድም ጊዜው የሚፈልግውን ፖለቲካ መረዳትንም በአጠቃላይ አዲስ ነገር የሌለው እየሆነ ነው። ስህተቶች ሲደጋገሙ ስላያን በይበልጥም በተቃዋሚዎቻችን መሀል መሻሻል እያየን ነው ብለን የምንደሰትበትን ወደ መቀራረብ የሚወስድ መከባበር የሚያደፈረስ ተንኳሽ የሆነ አካሄድ እየታዘብን ስለሆነ ያለፍላጎታችን የሱማሌ ጉዳይ ላይ ስለያዙት አቋም ወደኋላ እንድናስብ አድርጎናል። ህብረቱ ጠንካራ ሆኖ እንዲኖር እንፈልጋለን። ድርጅቱም ሆነ መሪዎቹ መኖራቸውን እንድናውቅ ግን ትግሉ ላይ በሚያበረክቱት በሚኖራቸው ድርሻ እንጂ የድርሻቸውን በመሰላቸው ከሚያበረከቱ ሌሎች ጋር በሚፈጥሩት አተካራ አይደለም። ትችታችን የሚያየውን በተቆርቋሪነት እንደሚገልጽ ዜጋ በትምህርታዊነቱ ቢወሰድልን ደስ ይለናል።

ዛሬ የትኛውንም ሱማሌ ስለሱማሌ ጉዳይ ካወራነው ኢትዮጵያ ላይ ያለውን ተቃውሞ ከአፉ ለመስማት የመለስን የሱማሌ ዘመቻ ደግመህ ደግመህ እንዲያምን አድርገህ በአገራቸው ጣልቃ ገብነቱን ማውገዝ ያስፈልጋል። ጠንካራ የጦርነቱም የመለስም ተቃዋሚ መሆንህን እርግጠኛ መሆን አለበት። ይህም ብቻ በቂ አይደለም ዘርህን ጠይቆ ማወቅ አለበት። ከዛ በኋላ ነው የመረረ እውነተኛ ስሜቱን የምታገኘው። ያለበለዚያ መስማት ትፈልጋለህ ብሎ ያሰበውን ነው የሚነግርህ። የኢትዮጵያ ጦር ሱማሌ መግባቱ ጥሩ ነው። ሰላም ሊያመጡልን ነው ይልሀል። ራዲዮ ጆሮው ላይ ይዞ በጉጉት እያዳመጠ 80% 90% አልሸባብ ተቆጣጠረ እያለ ሲፈነድቅ እየሰማህው። በአካል ሄዶ አገራቸውን ከወራሪ መከላከሉ ላይ ከመሳተፉ ጀምሮ በደንብ አድርገው በገንዘብ እንደሚረዱ እየታወቀ። ከዚህ በፊት ከሱማሌዎች ጋር ለኖረ፣ በስራ ምክንያት በህሪያቸውን ለሚያውቅ የዚህ አይነቱን ሚስጥራዊነት ፈጣን የባህሪ ለውጥ አደጋ እንዳለው ይገነዘባል። ይህን የባህሪ ለውጥ እንዴት አመጡት እግዚአብሄር ይወቀው። በደሉና ግፉ ከሆነ እኛን ለምን ውስብስብ አላደረገንም ። እንደውም ድሮ ነበርን አሉ። አበሻ እባብ ነው አይደል የሚባለው።

Sunday, August 2, 2009